Developmental Disabilities Administration (DDA)

# የመመዝገቢያ ግምገማ ማሳወቂያ

**Notification of Enrollment Review**

ቀን:

ስምና አድራሻ

የተወካዩ ስምና አድራሻ

ጉዳዩ: ለ______________________________ **የምዝገባ ግምገማ ማሳወቂያ**

በአሁኑ ጊዜ በአካል ጉዳተኞች አስተዳደር (DDA) ተመዝግበዋል። የDDA የምዝገባ ደንቦች በተለያዩ ጊዜያት የብቁነት ግምገማ ያስፈልጋቸዋል። ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ስር በDDA መመዝገብዎን ለመቀጠል ተጨማሪ መረጃ እንፈልጋለን። የአእምሮ ዝግመት፣ ሴረብራል ፓልሲ (በአእምሮ እድገት ላይ በሚደርስ ጉዳት የሚከሰት የሰውነት እንቅስቃሴን በአግባቡ ማዘዝ አለመቻልን የሚያስከስት ህመም)፣ የሚጥል በሽታ፣ ኦቲዝም (በአእምሮ ችግር ምክኒያት የሚከሰት)፣ ሌላ የነርቭ ወይም ከአእምሮ ዝግመት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ችግር። ምን ዓይነት መረጃዎች እንደሚያስፈልጉ እንድታውቅ የአስፈላጊ ዶክሜንቶች ሰንጠረዥን አያይዘነዋል።

**ምን ማድረግ ይጠብቅቦታል?**

DDA ይህንን ሁለተኛ ጊዜ የሚደረገውን የብቁነት ማረጋገጫ ሂደት በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለመላክ ደስተኛ ነው። DDA ለዚህ መረጃ እንዲልክ ከፈለጉ፣ እባክዎትን የተያያዘውን የስምምነት ፎርም እንደሚከተለው ይሙሉ።

1. በስምምነት ፎርሙ ላይ መረጃ ሊንጤይቅ የሚንችለውን የቦታዎች፥ አቅራቢዎች፥ እና ተቋማት ስሞችን ይፃፉ። በስምምነት ፎርም ላይ ለተዘረዘሩት ሁሉ የሚገኙበትን አድራሻ መረጃ ያካትቱ።
2. የተያያዘ(ዙ) የስምምነት ፎርም/ሞች) ላይ ፈርመው ቀን ይጻፉ፥ እንደዚሁም
3. ፎርሙን (ሞቹን) ለDDA ይመልሱ።

**ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ ምን ይከሰታል?**

ከእርስዎ ካልሰማን፣ በደንበኛ ፋይልዎ ውስጥ ያለውን መረጃ ተጠቅመን ብቁ መሆንዎን እንገመግመዋለን። የብቁነት ውሳኔውን ለማረጋገጥ በቂ መረጃ ከሌለ፣ በDDA ምዝገባዎ ይቋረጣል።

ማንኛውንም ዓይነት የአገልግሎት መቋረጥ እንዳያጋጥም በተቻልዎት መጠን በፍጥነት መልስዎትን ይላኩ፣ ነገር ግን ከዚህ በኃላ መሆን የለበትም ______________________.

በተጠቀሰው ቀን ውስጥ ምላሽዎ ካልደረሰን፥ በፋይልዎ ውስጥ ባለው መረጃ ላይ ተመርኩዘን የብቁነት ውሳኔ እናደርጋለን።

ጥያቄ ካልዎት፣ የሚከተለውን ያነጋግሩ፥

______________________________

የጉዳይ ሀብት አስተዳዳሪ ስም

______________________________

ስልክ ቁጥር

______________________________

የኢሜይል አድራሻ

ብቁነትን የሚቆጣጠሩ የስቴት ህጎች ቅጂ (WAC 388-823) በተጠየቀ ጊዜ ወይም በመስመር ላይ https://www.dshs.wa.gov/dda/consumers-and-families/eligibility ላይ ይገኛል።

ዓባሪዎች: የምዝገባ ማሟያ ሰንጠረዥ
የስምምነት ፎርም (DSHS 14-012)

ግልባጭ: የደንበኛው ፋይል

**የአስፈላጊ ዶኩምነቶች ሰንጠረዥ**

| የአካል ጉዳት ሁኔታ | ምርመራ | ምርመራውን የሚካሄደው ሐኪም | ሌሎች የተመዘገቡ መረጃዎች |
|---|---|---|---|
| የአእምሮ ውስንነት | የአዕምሮ ጉድለት ወይም ተመጣጣኝ ምርመራ | ፈቃድ ያለው ሳይኮሎጂስት፣ ዋሽንግተን የተረጋገጠ ትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት፤ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት በብሔራዊ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስቶች ማህበር የተረጋገጠ | ምርመራው ባለፉት 36 ወራት ውስጥ ከተጠናቀቀው ስታንዳረድ ዲቬሽን በታች ከሁለት በላይ የሆነ የመላመድ ችሎታ ፈተና ውጤት በምርመራ ሪፖርት መመዝገብ አለበት። |
| የአካል(አጥንት) እንደልብ ያለመታዘዝ እክል | ሴሬብራል ፓልሲ ወይም ተመሳሳይ የአንጎል ጉዳት ሙሉ በሙል ወይም በከፊል እጅና እግር ሽባ የሆነ | ፈቃድ ያለው ሐኪም፤ ፈቃድ ያለው የተፈጥሮ ሐኪም፤ ወይም ሐኪም ረዳት ወይም የላቀ የተመዘገበ ነርስ ፕራክቲሽነር (ARNP) ከነርቭ ልምምድ ጋር የተያያዘ። | ከሚከተሉት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት አካባቢዎች የዕለት ተዕለት ቀጥተኛ የአካል ድጋፍ አስፈላጊነትን የሚደግፍ መረጃ: መጸዳጃ ቤት፣ መታጠብ፣ መመገብ፣ ልብስ መልበስ፣ ተንቀሳቃሽነት ወይም ግንኙነት። |
| የሚጥል በሽታ | የሚጥል በሽታ ወይንም በድንገት ተከስቶ የሚጥል በሽታ | ፈቃድ ያለው የነርቭ ሐኪም | በህክምና ታሪክና በኒውሮሎጂካል ምርመራ ላይ የተመሰረተ ምርመራ፣ የህክምና ጣልቃገብነቶች ቢደረጉም ከሐኪም ወይም የነርቭ ሐኪም ቀጣይነት ያለው የሚጥል በሽታ ማረጋገጫ፣ እንደዚሁም የመላመድ ችሎታ ፈተና ከስታንዳርድ ዲቭሽን በታች ከሁለት በላይ ልዩነት ያለው ባለፉት 36 ወራት ውስጥ። |
| ኦቲዝም | ከፌብሩዋሪ 1፣ 2022 በፊት የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር ወይም ኦቲስቲክ ዲስኦርደር | ፈቃድ ያለው: ኒውሮሎጂስት፥ ሳይካትሪስት፥ ሳይኮሎጂስት፥ የእድገትና የባህርይ የሕፃናት ሐኪም፤ በWAC 182-531A-0200 እንደተገለጸው የልህቀት ማዕከል፤ ወይም ፈቃድ ያለው ሐኪም፣ ARNP፣ ሐኪም ረዳት፣ ወይም ከኦቲዝም ማዕከል ወይም የእድገት ማዕከል ጋር የተቆራኘ ናቱሮፓቲክ ሐኪም። | ምርመራው በምርመራ ዘገባ መመዝገብ አለበት፣ እና የመላመድ ችሎታ ፈተና ውጤት ካለፉት 36 ወራት ስታንዳርድ ዲቬሽን በታች ከሁለት በላይ ልዩነት ያለው። |
| ሌላ የነርቭ ወይም ሌሎቸደ ከአህምሮ ውስንነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የአእምሮ ችግረን የሚገልፅ መረጃ | የአስተሳሰብ ደረጃንና የመቀበል አቅምን የሚያጠቁ የነርቭ ወይም የክሮሞዞም አክሎች | ፈቃድ ያለው ሐኪም፣ ፈቃድ ያለው የናቱሮፓቲክ ሐኪም፣ የጄኔቲክስ ባለሙያ፣ ወይም ARNP ወይም ሐኪም ረዳት ከነርቭ ክሊኒክ ወይም የዘረመል መሞከሪያ ማዕከል ጋር የተያያዘ። | ብቃት ያለው ምርመራና የመላመድ ችሎታ ፈተና ውጤት ባለፉት 36 ወራት ውስጥ ከተጠናቀቀው ከስታንዳርድ በታች ከሁለት በላይ መደበኛ መዛባት። |
| **ማስታወሻ: ይህ ፎርም አጠቃላይ መመሪያ ብቻ ነው እናም DDA ተጨማሪ መረጃ ወይም ግምገማዎች ሊፈልግ ይችላል። ይህ ሰነድ ለምዝገባ ብቁነትን ለመወሰን የመጀመሪያው እርምጃ ነው። የDDA ምዝገባ የሚወሰነው በWAC ምዕራፍ 388-823 ነው።** | | | |